*የስብሰባው ዓይነት፡ የመስራች ጉባኤ የመክፈቻ ንግግር*
*ቀን፡ መጋቢት 15 2011*
*ቦታ፡ ካፒታል ሆቴል*

**የተከበራችሁ የፖለቲካ ፓርቲዎች መሪዎችና ተወካዮች**

**የተከበራችሁ የሲቪክ ማህበራት ኃላፊዎች**

**ውድ የብዙሀን መገናኛ ድርጅቶች ባለሙያዎች**

**የተከበራችሁ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አመራሮች**

**ክቡራን የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ አደራጆችና መስራች አባላት**

**ይህንን ፕሮግራም በቀጥታ የምትከታተሉ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የምትገኙ ኢትዮጵያውያን**

**ክቡራትና ክቡራን**

*ሀገራዊ ፖለቲካ*

ነጻነት፣ እኩልነትና ፍትህ፤

ሰላም፣እድገትና ብልጽግና

አንድነት፣ ብዝሀነትና መቻቻል፣

ኢትዮጵያውያንና መላው የሰው ልጆች ሁሌም የሚናፍቋቸውና የሚመኟቸው እሴቶች ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ በሀገራችን የረዥም ግዜ ታሪክ አብዛኛው ህዝባችን ሳይታደላቸው በርካታ ትውልድ አልፏል፡፡ ሰላም፣ ነጻነት፣ እኩልነት፣ ፍትህ በሌሉበት ሀገር ጠንካራ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት፣ አስተማማኝ ሰላም፣ የዜጎች የኑሮ መሻሻል፣ ሰርቶ መለወጥ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ማበብ ከቶም ሊታሰቡ አይችሉም፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ከምንም በላይ ሰላምና መረጋጋት የምትሻበት ግዜ ነው፡፡ ሰላማችንንና አንድነታችንን የሚፈታተኑ ጊዚያዊና ዘመን ተሻጋሪ አደጋዎች ተደቅነውባታል፡፡ የአብሮነት ታሪካችን እየተሸረሸሩ በጥቃቅን ምክንያቶች ልዩነቶች ሰፍተዋል፣ በብዙ የሀገራችን አካባቢዎች ግጭቶች ተበራክተዋል፣በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ከሚኖሩበት ቀየ ተፈናቅለው አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ይገኛሉ፡፡

በሀገራችን ለዘመናት ያልተፈቱና ከግዜ ወደ ግዜ እየተባባሱ ያሉ ችግሮች በርካታ ናቸው፡፡ ድህነት እና ስራ አጥነት፣ የዴሞክራሲና እና መልካም አስተዳደር እጦት፣ የፍትህ መዛባት፣ አግላይ የፖለቲካ ስርዓት፣  አድሎና ወገንተኛነት፣ ብሄርንና እምነትን መሰረት ያደረጉ አሰራሮች ከብዙ በጥቂቱ ናቸው፡፡የዘር፣ የጎሳና የኃይማኖት ብሄርተኝነት ህዝባችንን ከፋፍሎ አንድነታችንን አላልቶታል፡፡ በታሪካዊ ጉዳዮች ዙርያ ገንቢ ያልሆኑ ክርክሮች ተበራክተው የህዝባችን መሰረታዊ ችግሮች በሆኑት ድህነት፣ ስራ አጥነት፣ ርሀብ፣  ስደት፣ በሽታ፣ ወዘተ ላይ በርትተን እንዳንሰራ ኃይላችንን ከፋፍሎታል፡፡

ባለፉት ሁለት አስርተ ዓመታት በሀገራችንና በህዝባችን ላይ ተጭኖ በቆየው ብልሹና ኃላፊነት የጎደለው አስተዳደር በሀገራችን ውስጥ ግጭትና አለመረጋጋት እንዲስፋፋ፣ በዜጎች መካከል ጥርጣሬና አለመተማመን እንዲነግስ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ማንነትን መሰረት ያደረጉ አድሏዊ አሰራሮች እንዲስፋፉ ከፍተኛ አስተዋጾ አድርጓል፡፡ በዚህም በጣም ጥቂት የስርአቱ አባላትና ግብረ-አበሮቻቸው በከፍተኛ ሀብትና ንብረት ሲበለጽጉ ሰፊው የሀገራችን ህዝብ በድህነት፣ ርሀብ፣ ሞት፣ ስደት እየማቀቀ እንዲኖር ተገዷል፡፡ ስርዓቱን በሰላማዊ መንገድ ለመታገል ድምጻቸውን ያሰሙ ሰላማዊ እና ንጹሀን ዜጎች በሰው ልጅ ላይ ይፈጸማል ተብሎ በማይታመን ሁኔታ ተሰቃይተዋል፡፡ ከዓመት ዓመት ግፍ እና ሰቆቃው ሲበረታ በፖለቲካ አመለካከታቸው፣ በቋንቋ ወይም

ብሄራቸው፣ በሙያቸው ወይም በሀይማኖታቸው ምክንያት ጥቃት የደረሰባቸው ኢትዮጵያውያን በአንድነት ባደረጉት የተቀናጀ ትግል በሀገራችን አዲስ የተስፋ ጎህ ፈንጥቋል፡፡

የለውጥ ሂደቱን በተመለከተ

ከመጋቢት 2010 ጀምሮ በሀገራችን የተገኘው ውጤት የህዝብን ጥያቄ በጠመንጃ አፈሙዝና በሀይል ማስቆም እንደማይቻል በተግባር አሳይቷል፡፡ አንድ አመት ሊሞላው ጥቂት ቀናት የቀሩት የለውጥ ሂደት በርካታ ተስፋ ሰጪ ጅምሮች አስገኝቷል፡፡ የተጀመረው የለውጥ እንቅስቃሴ ኢትዮጵያውያን ለረዥም ዘመናት ለነጻነት፣ ለእኩልነትና ለፍትህ  የከፈሉት መስዋእትነት እና የጋራ ውጤት  በመሆኑ ሁሉም ዜጎች ከለውጡ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ስፈልጋል፡፡ ለውጡ በየትኛውም የህብረተሰብ ክፍል ላይ ስጋት እንዳይፈጠር ሁሉም ዜጎች የለውጡ አካል መሆናቸውን እንዲያስቡ ማድረግ የሚጠበቅ ሲሆን ሂደቱ እንዳይቀለበስም አፍራሽ ከሆኑ ተግባራት መቆጠብ ያስፈልጋል፡፡ ባለፈው አንድ አመት በተለያዩ አካባቢዎች በተነሱ ግጭቶችና እና የጸጥታ መደፍረስ እንዲሁም አንዳንድ የፌዴራል እና የክልል መስተዳድር አካላት በሚወስዷቸው ያልተጠኑና ወቅታቸውን ያልጠበቁ ውሳኔዎች ህዝባችን በለውጡ ማግስት የሰነቀው ተስፋ እያደር እንዲቀዛቀዝ አድርጎታል፡፡ ይሁን እንጂ ለውጥ **ሂደት በመሆኑ** የተስተዋሉ አስተዳደራዊ ግድፈቶች የለውጡን አስፈላጊነትና ትክክለኛነት ሊያስረሱንና ትልቁን ስእል ከማየት ሊያዘናጉን አይገባም፡፡

ቢያንስ ባለፈው ግማሽ ምእተ ዓመት ሀገራችን ብርካታ የለውጥ ጅምሮችን አስተናግዳለች፡፡ በለውጦቹ ማግስት ተስፋ ሰጭ እድሎች ቦግ ብለው ጠፍተዋል፡፡ የሀገራችን ፖለቲካ ከድጡ ወደ ማጡ እየሆነ ዛሬ ላይ ደርሰናል፡፡ለለውጦቹ መቀልበስ ዜጎች በተናጠልም ሆኑ በቡድን ለውጦቹን የተረዳንበትና ያስተናገድንበት መንገድ አንድ ምክንያት ሲሆን በሌላ መልኩ ለውጦቹ እንዳይሳኩ እና ሂደቱ ውስብስበ እንዲሆን የሚፈልጉ ኃይላት ህዝባችን የለውጦቹን ፍሬ ሳያጣጥም ወደ ባሰ እና የከፋ የፖለቲካ ስርዓት ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል፡፡ ዛሬ ላይ በሀገራችን የተጀመረው የለውጥ እንቅስቃሴ ስኬታማ ይሆን ዘንድ የታየው ወገገን ይበልጥ ይደምቅ ዘንድ ሁላችንም የድርሻችንን ልንወጣ ይገባል፡፡ ለውጥ “አለ” ወይስ “የለም” ከሚለው ውይይት ባሻገር አብዛኞቻችንን ሊያስማማ ወደሚችል ዴሞክራሲዊ ስርአት እንድንሸጋገር በተደራጀ መንገድ መታገል ይጠበቅብናል፡፡

## ከቡራትና ከቡራን

ሀገራችንን ከገጠሟት ወቅታዊም ሆኑ የረዥም ግዜ ችግሮች ለመላቀቅ የሁሉም ዜጎች የተናጠልና የጋራ ርብርብ ይጠይቃል፡፡ ከዚህ ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ኃይሎች ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ ዛሬ በይፋ የሚመሰረተው **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ሀገራችን ካሉባት ዘርፈ ብዙ ችግሮች ለመላቀቅ የድርሻቸውን አስተዋጾ ማድረግ በሚፈልጉ፣ የሀገራችን መጻኤ እድል፣ የህዝቦቿ ሰላምና እድገት ከምንም በላይ በሚያሳስባቸው ዜጎች የተቋቋመ ፓርቲ ነው፡፡**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በሀገራችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ የመልካም አስተዳደር መርሆች እንዲተገበሩ፣ የህግ የበላይነት እንዲረጋገጥና የፖለቲካ ስልጣን ከህዝብ የሚመነጭበት የፖለቲካ ባህል እንዲሰርጽ፣ ዜጎች ሀሳባቸውን በነጻነት የመግለጽ መብታቸው እንዲከበር፣ የሚዲያና የሲቪል ማህበራት በሀገር ግንባታ ውስጥ ሰፌ ሚና እንዲኖራቸው ይታገላል፡፡

አስተማማኝ ሰላምና ዘላቂ ልማት እንዲረጋገጥ፣ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች መካከል ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር፣ ለሀገራችን እና ለህዝባችን እድገት **“ነቀርሳ”** ሆኖ ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ እድገቷን በማቀጨጭ ላይ የሚገኘው ሙስና እንዲወገድ፣ የብሄረሰቦች ቋንቋና ባህል እንዲከበር፣ የሀይማኖት እና የአምልኮ ነጻነትና እኩልነት እንዲረጋገጥ፣ ጾታዊ መድሎ እንዲቆም፣ ሴቶች የትምህርትና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች ፍትሀዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እና በሀገር ግንባታ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ በትጋት ይሰራል፡፡

## የተወደዳችሁ የጉባኤ ተሳታፊዎች

ዜጎች አንደኛና ሁለተኛ ዜጋ በሚመስል መልኩ ሚናቸውና ተሳትፏቸው የተገደበባት ሀገር ሁሌም ውጥረት የነገሰባት፣ አንድነቷ የላላ፣ ደካማ እና የተከፋፈለች ከመሆኗም ባሻገር እድገቷን ለማይሹ የውስጥና የውጭ ኃይላት ተጋላጭ ትሆናለች፡፡ ብሄርን፣ ሀይማኖትን፣ ወይም ሌላ ማኛውም መስፈርትን መሰረት ያደረገ ኢ-ፍትሀዊ አሰራር ብሄራዊ አንድነታችንን ጭምር አደጋ ውስጥ ሊያስገባ የሚችል ስጋት በመሆኑ መላው የሀገራችን ህዝቦች በተለየም የፖለቲካ ሀይሎች ትኩረት ሊሰጡት የሚገባ አሳሳቢ ጉዳይ ነው፡፡ አፍሪካ እና መላው ዓለም እየተቀራረበና ጠንካራ ህብረት ለመመስረት እየታተሩ ባሉበት የ21ኛው ክፍለ ዘመን በጥቃቅን ምክንያቶች ተከፋፍለን መነታረክ የሀገራችንና እና የህዝባችንን አኩሪ ታሪክ የማይመጥን ሀገራዊ ክብራችንን የሚቀንስ በመሆኑ ልዩነታችንን አክብረንና ብዝሀነትን ተቀብለን በአንድ ሀገር በሰላምና በፍቅር መኖር ብቸኛ አማራጭ ነው፡፡

አንድነቷ የተጠበቀ የተከበረችና የበለጸገች ሀገር ከምንም በፊት በዜጎቿ መካከል ፍትህን ልታሰፍን የግድ ነው፡፡ አንድ እናት ከአብራኳ  በወጡ ልጆቿ መካከል ልታበላልጥ እንደማትችል ሁሉ፣ ኢትዮጵያም ልጆቿ በብሄር፣ በቋንቋ፣ በሀይማኖት፤ በፖለቲካ አመለካከት፤ በአካባቢ፤ በጾታ፤ ወዘተ ሳይለያዩ ሁሉም የኢትዮጵያ ልጆች በሀገራቸው ጉዳይ እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ የሚሆኑበት የፖለቲካ ስርአት መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ድህነት የሌለባት የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመገንባት የፍትህ መስፈን ወሳኝና ግንባር ቀደም ጉዳይ መሆኑን የሚያምነው **የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በዜጎች መካከል ፍትህ እንዲሰፍንና በማንኛውም መልኩ አድልዎ እንዲወገድ ይጥራል፡፡

በሀገራችን ፖለቲካ ውስጥ የአካታችነትና አሳታፊነት እሳቤ በእጅጉ ደካማ ነው፡፡የሀገራችን ህጎችና ፖሊሲዎች ሲረቀቁ እና ሲጸድቁ መላው የሀገራችን ህዝቦች ፍላጎትና ሀሳብ የሚያካትት እንዲሆንና የጥቂት የፖለቲካ ልሂቃን ፍላጎትና በሌሎች ላይ እንዳይጫን ግልጽ እና አሳታፊ የፖለቲካ ስርአት ያስፈልገናል፡፡ እስከአሁን ድረስ በሀገራችን ያለው አሰራር ስልጣን የተቆጣጠሩ ጥቂት ፈላጭ ቆራጮች ሰፊውን የሀገራችን ህዝብ ፍላጎት፣ ስጋት፣ ጥቅም፣ ሀሳብ፣ ጥያቄ ችላ ብለው ያሻቸውን ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ህዝብና መንግስት ሁሌም ሆድና ጀርባ እንደሆኑ ዛሬ ላይ ደርሰናል፡፡ የመንግስት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች የዜጎችን ሰብአዊና ዴሚክራሲዊ መብቶች የሚያስጠብቅና የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸውን የሚያረጋግጥ እንዲሆን ነእፓ ይታገላል፡፡

**ውድ የጉባኤው ተሳታፊዎች**

ግልጽ እና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ለአንድ ሀገር የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ዋና ማሳያ ነው፡፡ ዜጎች መሪዎቻቸውን በነጻነትና በፍቃደኝነት የመምረጥ እድል ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የምርጫ ሂደትና ውጤቶች በመራጩ፣ በተፎካካሪዎችና በታዛቢዎች  ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል፡፡የሀገራችን የምርጫ ስርአት እና ታሪክ በየትኛውም መመዘኛ ከዚህ የራቀ ነው፡፡ ሐገራችን አንድ ፓርቲ ከራሱ ጋር ተወዳድሮ የሚያሸንፍበት በርካታ ምርጫዎችን አስተናግዳለች፡፡ ይህ ታሪክ ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ ሊቆም ይገባል፡፡ ከእንግዲህ በሀገራችን የሚካሄዱ ሀገር አቀፍና የአካባቢ ምርጫዎች ሰላማዊ፣ ነፃ፣ ፍትሐዊና ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን ለማድረግ መንግስት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚጠበቅባቸውን ሁሉ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች

የሀገራችንን ምጣኔ ሀብት ስንመለከት ኢትዮጵያ ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት፣ ውብ መልክአ ምድር፣ ለማልማት ምቹ የተፈጥሮ ሀብቶች፣ ለግብርና ተስማሚ የእርሻ ቦታዎች፣ ለመስኖ የሚውሉ ወንዞችና ጅረቶች አሏት፡፡ኢትዮጵያ በአለም ብርቅየ የዱር እንሰሳትና አእዋፋት፣ ለቱሪስት መስህብ የሆኑ ተራሮችና ደኖችና እድሜ ጠገብ ቅርሶች መገኛ ናት፡፡ ከግማሽ በላይ የአትዮጵያ ህዝብ በወጣቶች የተገነባ ሲሆን በቂ ትምህርትና ስልጠና ማግኘት ቢችሉ ለሀገራችን ሁለንተናዊ እድገት ከፍተኛ አስተዋጾ

ማበርከት ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ የተትረፈረፈ የተፈጥሮ ሀብት ያላት ሀገራችን ከአለም ድሀ ሀገሮች ተርታ የምትመደብ ሲሆን ተፈጥሮ የቸረንን ጸጋ ከማድነቅና ከዘፈን ያለፈ ስራ ሳንሰራ በርሀብ እና እርዛት ውስጥ እንማቅቃል፡፡

በዜጎች መካከል የሀብት ክፍፍል እጅግ እየተራራቀ መጥቷል፡፡ በክልሎች መካከል ያለው የእድገት ሁኔታም ከግዜ ወደ ግዜ እየሰፋ ይገኛል፡፡ ፍትሀዊ ያልሆነ የሀብት ክፍፍል እና ኢ-ፍትሀዊ እድሎች መኖር የግጭት መንስኤ ሲሆን የሀገርን ሰላምና መረጋጋት በከባዱ ያውካል፡፡ በመሆኑም ሁሉም ኢትዮጵያውያን ለስራ እና ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች እኩል እድል እንዲኖር የሚያረጋግጥ ስርአት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ከፍተኛ የማደግ አቅም ላለው የሀገራችን ኢኮኖሚ ሰፊ ገበያ ለመፍጠርና በዓላማ ዓቀፍ የገበያ ሰንሰለት ውስጥ ተገቢ ስፍራ እንዲኖረን ለማድረግ አካባቢያዊና አህጉራዊ የገበያ ትስስርን ማጠናከር፣ መደገፍና ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡በቴክኖሎጂ በመታገዝ በፍጥነት እየሰፋ በመጣው የግሎባላይዜሽን ስርአት ውስጥ በጠንካራ መሰረት ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚ መገንባት ካልቻልን በዓለም አቀፍ የንግድ ውድድር ተሸናፊ እንሆናለን፡፡ በመንግስትና በግል ሴክተሩ ውስጥ ሰፊ የስራ እድል በመፍጠር ስራ አጥነትን መቀነስ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት በሀገር ደረጃ በሚሊዮን የሚቆጠር የስራ እድል መፍጠር ካልቻልን ድህነትን የማጥፋት ህልማችን ፍሬ ቢስ ሆኖ የሚቀር ሲሆን ስራ ፍለጋ ባህር አቋርጠ የሚሰደዱ ዜጎችን ማስቆም አንችልም፡፡ ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ከድህነት የማውጣት ተስፋ ሰንቀው ለስራ ፍለጋ ከሀገራቸው የወጡ እህቶቻችንና ወንድሞቻችን በባእድ ሀጋር ሲሰቃዩና ሰብአዊ መብታቸው ተዋርዶ የምናይበት ግዜ ሊያቆም ይገባል፡፡የስራ አጥነት ችግር ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮት ብቻ ሳይሆን ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳይ ነው፡፡ በተለይም በወጣቱ የህብረተሰቡ ክፍል የተንሰራፋው ስራ አጥነት ሀገራችንን ከገጠሟት ብሄራዊ ስጋቶቸ አንዱ ሆኗል፡፡

ተባብረን ሰርተን የሀገራችን መጠፎ መገለጫ የሆነውን ድህነትን በማጥፋት የሀገራችን ህዝቦች ኑሮ እንዲሻሻል ማድረግ የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ  ተቀዳሚ ተግባር ይሆናል፡፡ ይህ ሲሆን <u>ድርቅ፣ ርሀብና ችግር</u> ተወግዶ የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ከዓለም ፊት ቆመን ከመለመንና እጃችንን ከመዘርጋት እንድናለን፡፡ ይህን ማድረግ ስንችል <u>ኢትዮጵያ እጆቿን ለፈጣሪ ትዘረጋለች </u>የሚለውን ኢትዮጵያዊ አስተምህሮ እውን ማድረግ እንችላለን፤ ራሳችንን ቀና አድርገን ከዓለም ፊት እንቆማለን፡፡ ከኛ ኃላ ለሚመጣው ትውልድ በሀገሩ ኮርቶ እንዲኖር መሰረት አስቀምጠን ማለፍ ብቻ ሳይሆን ከታሪክ ተጠያቂነት እንድናለን፡፡

የውጭ ግንኙነት

**ውድ የጉባኤ ተሳታፊዎች**

ሀገራችን ከአፍሪካ፣ ከአውሮፓ፣ ከአስያ፣ እንዲሁም ከመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ጋር ረዥም ታሪክ ያለው ጠንካራ ግንኙነት አላት፡፡ ከእነዚህ ሀገረሮች ጋር ከፍተኛ የንግድ፣ የባህልና የዲፕሎማሲ ስራዎች እንሰራለን፡፡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎቻችን በእነዚህ ሀገራት ውስጥ በስራ፣ በትምህርት በሌሎች ምክንያቶ ይኖራሉ፡፡ ባንጻሩ የብዙ ወዳጅ ሀገሮች ህዝቦች በሀገራችን ውስጥ በተለያዩ የስራ መስኮች ተሰማርተው ይሰራሉ፡፡ በተለያየ ግዜ በስልጣን ላይ የቆዩ መሪዎች የሀገራችንን ጥቅም ለባእድ ኃይላት አሳልፈው የሰጡበት አጋጣሚዎች ቀላል አይደሉም፡፡ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር የተሻለ ግንኙነት መፍጠር እና የህዝቦችን የጋራ ተጠቃሚነት ይበልጥ ማሳደግ የሚቻልበትን እድሎችን በሚገባ የመጠቀም ቅንነትና ዝግጁነት አልነበራቸውም፡፡ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** የውጭ ግንኙነት ፖሊሲያችን የሀገራችንንና የህዝቦቿን ጥቅም የሚያስከብር፣ በሌሎች ሀገሮች በተለይም በጎረቤቶቻችን የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ባለመግባትና ማንም የውጭ ሀይል በውስጥ ጉዳያችን ጣልቃ እንዳይገባ እንዲሆን ሳያለስልስ ይሰራል፡፡ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችን ዋነኛው የትኩረት አቅጣጫ ይሆናሉ፡፡

**የተከበራችሁ የሀገራችን ህዝቦች**

የህግ የበላይነትን ማስከበር አስፈላጊ እና ተገቢም ነው፡፡ ይሁን እንጂ ያለበቂ ጥናትና ውይይት የዜጎችን ኑሮ የሚያናጉ፣ ቤተሰብን ለአደጋ የሚያጋልጥ የህጻናትን ስነልቦና የሚጎዳ፣ የወላጆችን ቅስም የሚሰብር፣ የተቻኮለ ውሳኔ የህዝቦችን አንድነትና የሀገርን ሰላም ሊያውክ ሲለሚችል በኃላፊነትና እና በከፍተኛ ጥንቃቄ ሊካሄድ ይገባዋል፡፡ በሀገራችን አንዳድ አካባቢዎች የመንግስት አካላት በሚወስዷቸው ውሳኔዎች የሚፈሰው የህዝብ እንባ ሀገራችን ያለችበትን ስስ እና ውስብስ የለውጥ ጉዞ ይበልጥ እንዳያወሳስበው በመንግስት የሚወሰዱ ማናቸውም ውሳኔዎች በሰከነ እና ሊፈጥሩ የሚችሉትን ተጽእኖ ታሳቢ ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡

**የተወደዳችሁ አባላት፣ ክቡራን እንግዶች**

ኢትዮጵያውያን ለእምነት ከፍተኛ ዋጋ እንሰጣለን፣ ለኃይማኖታዊ አስተምህሮ፣ ለእምነት ተቋማትና ለኃይማኖት ምሁራን ከፍ ያለ አክብሮት አለን፡፡ ሁሉም እምነቶች ስለሰው ልጆች ወንድማማችነት እና እህትማማችነት፣ ቅንነት፣ ፍትህ፣ መተዛዘን፣ ይሰብካሉ፡፡<u>**ክርስትና ፍቅርን ያስተምራል ኢስላም ሰላምን**</u>፡፡ ይሁን እንጂ ዛሬ እኛ ሁሉንም አጥተናል፡፡ ሰላም ወዳድነታችን **ነብይ የመሰከሩላት ሀገራችን** ኢትዮጵያ ዛሬ ሰላሟ ከፉኛ ተነሳቅሎ ልጆቿ በስጋት ድባብ ውስጥ እየኖሩ ይገኛሉ፡፡ በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች በሀገራቸው ሰላም አጥተው ወደ እኛ ለተሰደዱ ሰዎች ከለላ እና ድጋፍ እንዳልሆንን ባላፉት አስርት ዓመታት ኢትዮጵውያን በሀገራቸው ሰላም አጥተው <u>በባእድ ሀገር የመከራ ህይወት የሚገፉ ብዙዎች ናቸው</u>፡፡ ሀይማኖታዊ እሴቶቻችንን ለአብሮነት፣ ለአንድነትና ለሰላም ብንጠቀም ለእምነት አባቶቻችንን ምክርና ትምህርት ጆሮ ብንሰጥ ሰላማችንን አብሮነታችንን ለማጠናከር ትልቅ አስተዋጾ ይኖረዋል፡፡

የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ከልዩነት ይልቅ አንድነት፣ ከመከፋፋል ይልቅ መሰብሰብ፣ ከጥላቻ ይልቅ ፍቅር፣ ከግጭት ይልቅ ሰላም፣ ከመወጋገዝ መተጋገዝ፣ ከጥርጣሬ ይልቅ መተማመን እንዲሰፍን በመላው የሀገራችን ክፍል ዘላቂ ልማት፣ አስተማማኝ ሰላምና መረጋጋት፣ እውነተኛ ህትማማችነት እንዲነግስ ይሰራል፡፡ የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ መልእክት ሰላም ነው ሰላም ለሀገራችን ሰላም ለጎረቤቶቻችን ሰላም ለኬንያ፣ ሰላም ለሱዳን፣ ለጂቡቲ፣ ለኤርትራ፣ ለሱማሌ፣ ሰላምና ብልጽግና ለአፍሪካ እና ለአለም ህዝቦች ሁሉ፡፡

በመጨረሻም ጥሪያችንን አክብራችሁ በዚህ ታሪካዊ ቀን በመሀከላችን ለተገኛችሁ ውድ እንግዶቻችን፣ ጉባኤውን ለመዘገብ እና የሰላም፣ የአንድነት፣ የወንድማማችነት፣ የመቻቻል መልእክታችን ለመላው የሀገራች ህዝብ እንዲደርስ ለማድረግ ለታደማችሁ የመገናኛ ብዙሀን ባለሟሎች፣ የፓርቲ ምስረታ ስራዎቻችን የተሳኩ እንዲሆን አስተዳደራዊ ድጋፍ ላደረጉልን የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ኃላፊዎችና ሰራተኞች፣ ጠቃሚ ልምዳቸውን ላካፈሉንና ምክራቸው ለለገሱን የፖለቲካ ፓርቲዎች በመላው የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ስም ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

አመሰግናለሁ፡፡